መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
አቅራቢዎች

# የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: M. Maillot

ያሻሻለው (አሻሽሎ የጻፈው): E. Frischbutter; Sarah S.

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2013 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ከብዙ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ድንግል ወደ ሆነችው ማሪያም ወደምትባል አይሁዳዊት ሴት መልአኩ ገብርኤልን ላከው።




እንዲህ አላት “ድንግል ትፀንሻለሽ
ወንድልጅም ትወልጃለሽ ሰሙንም
እየሱስ ብለሽ ትጠሪዋለሽ፤
እሱም የእግዚአብሔር
ልጅ ይባላል
ለዘለዓለምም
ይነግሣል።”

“ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?”
በሚል ይህች ሴት ጠየቀችው።
“ከማንም ሰው ጋር
አልነበርኩም አላቸው”
መልአኩም
ህፃኑ የመጣው
ከእግዚአብር
ዘንድ ነው።



ከሰው አባት የተገኘ
ልጅ አይደለም አላት።



መልአኩም ለማሪያም እንዲህ አላት
ዘመድሽ ኤልሳቤጥም
ፀንሳለች።



ይህ ተአምር ነው ብሎ ማርያምም
ዘመዷን ኤልሣቤጥን
ልትጎበኛት ሄደች።
ሁለቱም በጋራ
እግዚአብሔርን
አመሠገኑ።



ማሪያም ዮሴፍ ለሚባል
ሰው ታጭታ ነበር።
ማሪያምም እንደፀነሰች
በሰማ ጊዜ ዮሴፍም
በጣም አዘነ።
ከሌላ ሰው
ልታረግዝ
እንደምትችልም
አሠበ።



መልአኩም በህልም
ተገልጠለት ዮሴፍ ሆይ ይህ ህፃን
የተፀነሰው በሰው ፈቃድ ሳይሆን
በእግዚአብሔር ነውና ማሪያምን
ለመውሰድ አትፈራ አለው።



ዮሴፍም ማሪያም ይረዳት
ነበር ህፃኑን እንሱስንም
ይንከባከበው ነበር።





ዮሴፍም እግዚአብሔርን አመነው
ታዘዘውም በተጨማሪም
የሃገሪቱን ህግ
ይታዘዝና

ለህጉም ይገዛለት ነበር ...

... ምክንያቱም አዲስ ህግ ከመውጣቱ
የተነሣ ማሪያና
ዮሴፍ ሃገራቸውን
ለቅቀው ...



… ወደ ሌላ ሃገር ተሰደዱ
ቤተልሄምም በደረሱ
ጊዜ ታክስ (ግብር)
ከፈሉ።




ማሪያም
ልጅ የመውለጃዋ
ጊዜም ደረሠ
ነገር ግን ዮሴፍ
የምትወልድበትን
ምቹ ...


… ቦታ ሊያገኝ
አልቻለም ሁሉም
ክፍት የሚመስሉ
ቦታዎች ሁሉ
ሞልተው ነበር፡፡

ዮሴፍም በመጨረሻው የከብቶች በረት አገኘ በዚያም ህፃኑ እየሱስ ተወለደ።



እናቱም ህፃኑን በከብቶች
በረት ውስጥ አስተኛችው።



ይህ ሥፍራ የእንስሳት ማደሪያና
መኖአቸው የሚቀመጥበት
ሥፍራ ነው።



በአቅራቢያው መንጋቸውን የሚያሠማሩ
እረኞች ነበሩ የእግዚአብሔር
መልአክም ...



... ወደ እነርሱ ቀርቦ ድንቅ
ዜና የምሥራች ነገራቸው።




ዛሬ በደዊት ከተማ አዳኝ የሆነው
ክርስቶስ ኢየሱ ተወልዶላችኋል
ህፃኑም ...

... በከብቶች በረት በግርግም ተኝቶ
ታገኙታችሁ ብሎ ነገራቸው።




ወዲያው የሚያበሩ መልአክትም
ተገልጠው እግዚአብርሔን
እንዲህ እያሉ
ያመሰግኑት
ነበር
ክብር ...


… በላይ በሠማይ በታችም በምድር
ለእግዚአብሔር ይሁን ሰላምና
በጎ ፈቃዱ
በምድር
ይሁን አሉ።


እረኞቹም እየሮጡ የተባለበት
ሥፍራ ደረሱ ህፃኑንም ካዩት
በኋላ ላገኙት ሰው ሁሉ ...


... መልአኩ ስለ ኢየሱስ
(ስለህፃኑ) የነገራቸውን ሁሉ
እውነት እንደሆነ መናገር ጀመሩ።



ከ40 ቀናትም በኋላ
ማሪያምና ዮሴፍ ህፃኑን
ወደ ኢየሩሳሌም
ቤተመቅደስ
መልሠው አመጡት
ስምኦን የሚባል
ሰውም አገኙ
እሱም ስለህፃኑ
እግዚአብሔርን
አመሠገነ ሌላው ...



... የእግዚአብሔር
አገልጋይ ሃናንያ
የሚባል ሰውም
ለእግዚአብሔር
ምሥጋናን
አቀረበ።



ሁለቱም ኢየሱስ
የእግዚአብር ልጅ
እንደሆነ ያውቁ
ነበር፣ ሊመጣ
ያለው መሲህ ነው
አሉ። ዮሴፍም
2 ወፎችን
መሥዋዕት
አደረገ።



ይህም እግዚአብሔር
ከሠጣቸው ህግ
ውስጥ አንድ ሰው
ልጅ ሲወልድ
ማቅረብ ያለበት
መሥዋት ነው።


ከጥቂት ጊዜያት
በኋላም አንዲት
ኮከብ ጠቢባንን
እየመራች
ህፃኑ ተወለደ ወደ
ተባለበት ወደ ኢየሩሳሌም
አደረሰቻቸው።



“የተወለደው የአይሁ ንጉሥ ወዴ አለ?” ሲሉ ጠየቁት

“እሱንም ልናመልከው እንፈልጋን አሉ።”

እኝህ ጠቢባን ሠዎች ያሉትን ሁሉ ንጉሡ ሄሮዲስ ሰማ። እሱም ተረበሸና እየሱን መቼ እዳገኙት ጠየቃቸው “እኔም እሱን ላመልከው እፈልጋለሁ” አላቸው።



ነገር ግን ውሸቱን
ነበር ሊገድለው
ይፈልግ ነበር።




ከህፃኑ ልጅ ጋር ወደ ሚኖሩበት ወደነ
ማሪያም ቤት ኮከቧ ጠቢባንን
መርታ አደረሠቻቸው
ወድቀው ከሠገዱለት በኋላ
ያመጡለትን
የከበረ ስጦታ
እጅ መንሻ
ለህፃኑ ሰጡት።።

እግዚአብሔር ለጠቢባን
በማስተዋል ወደቤታቸው
እንዲመለሱ ነገራቸው።



ሔሮዲስም ስለ ተቆጣ
ህፃኑንም ሊገድለው
ወስኖ ነበርና።



በቤተልሄም የሚገኙትን
ወንድ ህፃናቶች በሙሉ
አስገደለ።



ነገር ግን ሄሮዲስ
የእግዚአብሔርን
ልጅ ሊያገኘው
ፈጽሞ አልቻለም።





በዚህም
አስጠነቀቃቸው
“ዮሴፍ ማሪያምን
ይዘው ወደ ግብፅ
አገር ሂድ” አለው።

ንጉሤ ሄሮድስም
ከሞተ በኋላ
ዮሴፍ ሚስቱን



ማሪያምንና
ኢየሱስን ከግብፅ አገር
ወደ ቤተልሄም መልሶ ይዟቸው መጣ።

እነሱም በገሊላ
ባህር አጠገብ
በምትገኝ



ናዝሬት በምትባል
ትንሽ ከተማ ውስጥ ይኖሩ ነበር።

# የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

የማትዎስ ወንጌል ከምዕራፍ 1-2
እና የሉቃስ ወንጌል ከምዕራፍ 1-2

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን
ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን
በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር
እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው
ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና
ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት
እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ
በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን
እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር
እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል።
እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ
ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ
ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ
አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ሰትል
ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ
ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን
ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር
ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ
ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ
ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16